# ጋዜጣዊ መግለጫ

## የአሜሪካ ኤምባሲ

አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ

ለበለጠ መረጃ በ 011-130-7033 ይደውሉ
http://et.usembassy.gov/

*2017/14*

---

**የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ተራድኦ ድርጅት (USAID) 18.4 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ መገልገያ መሣሪያ ለገሰ**

***አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ፤ ሰኔ 13፤ 2009፡-*** የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ተራድኦ ድርጅት (USAID) ዛሬ በእንሰሳት ግብይት ልማት በኩል በአማራ፤ ኦሮሚያ፤ ደቡብ እና ትግራይ ክልሎች ለሚገኙ 24 ተጠቃሚዎች 800,000 ዶላር (18.4 ሚሊዮን ብር) የሚያወጣ የወተት ተዋጽኦ ማቀነባበሪያ መሣሪያ ልገሳ አደረገ። የቁሳቁስ ልገሳው በሺዎች የሚቆጠሩ ባለአነስተኛ ማሣ አርሶ አደሮች ለምርታቸው አስተማማኝ ገዢዎችን ሲያስገኝላቸው፤ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩትን ደግሞ በተገቢው መንገድ የተቀነባበረ የወተትና የሥጋ ውጤቶች ተጠቃሚ ያደርጋቸዋል።

በልገሳ ከተሰጡ መሣሪያዎች ውስጥ፤ የወተት ተዋጽኦ ማሸጊያ ማሺኖች፤ የወተት ፓምፖች፤ ማቀዝቀዣ ጋኖች እና ፓስቸራዘሮች እንዲሁም ማፍያ መሣሪያዎች፤ የሥጋ እና ወተት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች፤ የወተት መፈተሻ መሣሪያ፤ የእንሰሳት የክብደት መለኪያ እና ተንቀሳቃሽ ልኳንዳ ቤት ሲገኙበት፤ ይህም በUSAID ከሚለገሰው የ1.9 ሚሊዮን ዶላር ጠቅላላ ድጋፍ አካል በመሆን፤ በተጠቃሚዎች የሚደረገውን የ4.2 ሚሊዮን ዶላር ኢንቨስትመንት ይደግፋል።

የእንስሳት እና አሳ ሃብት ልማት ሚኒስትር ፕሮፌሰር ፈቃዱ በየነ እና የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ተራድኦ ድርጅት (USAID) የኢትዮጵያ ዳይሬክተር ሌስሊ ሪድ፤ ከግሉ ዘርፍ፤ ከፌደራልና የክልል መንግሥታት ፤ የልማት አጋሮች እንዲሁም ዘርፍ-ተኮር ማኅበራት እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ተወካዮች በተገኙበት መሣሪያዎቹን ለተጠቃሚዎች አስተላልፈዋል።

ሌስሊ ሪድ በርክክብ ስነስርዓቱ ባደረጉት ንግግር፤ "የዛሬዎቹን ተጠቃሚዎች ጨምሮ፤ የእንስሳት እና አሳ ሃብት ልማት ሚኒስቴር እና ሁሉም የግሉ ዘርፍ ባለድርሻ አካላት በጋራ በመሥራት የእንሰሳት ሀብት ኢንዱስትሪው የብዙዎችን ሕይወት በመቀየር እና የኢትዮጵያን የምጣኔ ሀብት የማያቋርጥ ጠንካራ መሠረት እንዲኖረው በማስቻል አስተማማኝነቱ የተረጋገጠ እና ይበልጥ ትርፋማ እንዲያደርጉት ጥሪዬን አቀርባለው" ብለዋል። ዳይሬክተሯ አክለውም "በኢትዮጵያ የእንሰሳት እና የወተት ተዋጽኦ ዘርፎችን ለማሳደግ በመንግሥት እና በግሉ ዘርፍ ለሚደረጉ ጥረቶች የሚናደርገውን ትብብር እና እገዛ በቀጣይነት የማጠናከር ፍላጎት አለን" ሲሉ ገልጸዋል።

ወተት እና ሥጋን በማምረት፤ በማደራጀት እና በማቀናበር ሥራ የተሰማሩ የኅብረት ሥራ ማኅበራት እና የግል ድርጅቶች የድጋፉ ተጠቃሚዎች ሲሆኑ፤ የቁሳቁስ ድጋፉ መንግሥት በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ፤ የሀገሪቱ የእንሰሳት ሀብት ዘርፍ እመርታ እንዲያሳይ የሚያደርገውን ጥረት የሚደግፍ እና USAID በእንሰሳት ሀብት ዘርፍ የሚያደርገው አስተዋጽኦ ጉልህ ማሳያ ነው።

የUSAID የእንሰሳት ግብይት ልማት፤ በአራት ክልሎች የሚገኙ አነስተኛ ማሣ ያላቸውን አርሶ አደሮች ገቢ እና የስነ-ምግብ ደረጃ ለማሻሻል ያለመ፤ የአሜሪካ መንግሥት መጪውን ትውልድ መመገብ (Feed the Future) ዕቅድ አካል የሆነ የአምስት ዓመት መርሃግብር ነው።

\# # #